# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 242 ታህሳስ 25 2005 ገጽ 1


ሁሌም ህዝብ አሸናፊ ነው፤ ሙባረክ በአለም አለ የሚባል የጦር ሰራዊትና የቴክኖሎጅ ብዛት የነበረው አምባገነን መሪ ነበር፤ ጋዳፊ የመከላከያ ጡንቻቸውን በቴሌቪዥን መስኮቱ ደጋግመው ለአለም ሲያሳዩ ሲኮፈሱ ነበር፤ ከቶ የአንዱም የሰራዊት ሃይል የህዝብ ቁጣ ማእበልን ሊገታው፣ ሊያቆመው አልተቻላቸውም። ታዲያ የኛዎቹ ትንሽዬ አምባገነን ዘረኛ መሪዎች ምን ሽቷቸው ይሆን የሰራዊት ህብረ-ትርኢት ማሳየት የጀመሩት?

ከግንቦት 7 ዕርስ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ኢትዮቴሌኮም የወያኔ ዘረኝነት ፖሊሲ መንጸባረቂያ መሆኑን የግንቦት ሰባት የአገር ዉስጥ ኢንተሊጀንስ አጋለጠ

የመረጃ ቴክኖሎጂ መሠረት የሆነዉ የቴሌኮሚኒኬሺን ዘርፍ አፍሪካ፤ ላቲን አሜሪካና ኢሲያ ዉስጥ የሚገኙ በእደገት ወደ ኋላ የቀሩ አገሮችን ለዘመናት ከተዘፈቁበት የኋለ ቀርነት ማጥ ዉስጥ ጎትቶ አዉጥቶ ወደ ፈጣን የእድገት ጎዳና ይወስዳቸዋል ተብሎ የታመነበትና በአንዳንድ አገሮች ዉስጥ ይህ ለእድገት አመቺነቱ በተግባር የተመሰከረለት ዘርፍ ነዉ። ይህ ዘርፍ ገበሬዉ፤ ሰራተኛዉ፤ ተማሪዉ፤ ወታደሩና ለሌላም በማንኛዉም የስራ ዘርፍ ለተሰማራ የህብረተሰብ ክፍል የእዉቀት ምንጭ በመሆን የስራ ምርታማነቱን እንዲያሳድግ የሚረደና በህብረተሰብ መካከል ፈጣን የሆነ የመረጃ ልዉዉጥ እንዲኖር የሚያደርግ ዘርፍ ነዉ።በእድገት ወደ ኋላ ለቀረችዉ አገራችን ኢትዮጵያም ይህ ዘርፍ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ ዘርፍ ነዉ። ነገር ግን በአፍሪካ ዉስጥ አገራችን ኢትዮጵያ እጅግ በጣም ወደኋላ ከቀረችባቸዉና ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ ሆን ብሎ እድገታቸዉ እንዲገታ ካደረጋቸዉ ኋላ ቀር ዘርፎች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ ይሄዉ የቴሌኮሚኒኬሺን ዘርፍ ነዉ።

እራሱን "ልማታዊ መንግስት" ብሎ የሚጠራዉ የወያኔ አገዛዝ ስልጣን ከያዘባቸዉ የመጀመሪያዎቹ አመታት ጀምሮ እስከ ቅርብ ግዜ ድረስ እንደ ቤት ዉስጥ ዕቃዉ ከተቆጣጠራቸዉና የኢትዮጵያን ህዝብ በሚጠቅም መልኩ እንዳያድጉ ካደረጋቸዉ ቁልፍ መስሪያ ቤቶች ዉስጥ አንዱ ኢትዮቴሌኮም ነዉ። ወያኔ ኢትዮቴሌኮምን ያላደረገዉ ነገር የለም። ዘረኝነትን በሚጠቅም መልኩ አደራጅቶታል፤ የራሱን ሰዎች ጠቅጥቆበታል፤ ቻይናዎችን አምጥቶ የስለላ ተቋም አድርጎታል፤ የሚገርመዉ ዛሬ ኢትዮቴሌኮም የተራቀቀዉ በስልክ፤ በኢንተርኔትና በሌሎችም የመገናና አገልግሎቶች ሳይሆን ዜጎችን በመሰለልና የመረጃ ጨለማ በመፍጠር ርካሽና ጎታች ስራዎች ነዉ። ይህንን ርካሽ ስራ ደግሞ በቅርቡ የአገዛዙ የኢንፎርሜሺን ደህንነት ኤጀንሲ ሹም ብ/ጄኔራል ተክለብርሃን ወልደአረጋይ "የኢትዮጵያ ቴሌኮምኒኬሽን" የኀብረተሰቡን ሰላም የሚያጠፉ ዌብሳይቶችን የመቆጣጠርና የኢንተርኔት ድረገጾችና ብሎጎችን የማገድ አቅም ሊኖረው ይገባል:: መርሁም ይህ ነዉ በማለት በአዳባባይ አረጋግጧል።

የግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የአገር ዉስጥ ኢንተሊጀንስ ዘርፍ በላፉት ስድስት ወራት ይህንኑ ኢትዮቴሌኮም በሚል መጠሪያ የሚታወቀዉንና በስለላ ስራ ላይ የተሰማራዉን የሲቪል መስሪያ ቤት አደረጃጀት፤ አወቃቀርና የሰዉ ኃይል አመዳደብ በቅርብ ተከታትሎ ከዚህ ቀትሎ የሚታየዉን መረጃ አጠናቅሯል።(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በኢትዮጵያ የተለያዩ ከተሞች ከፍተኛ አለመረጋጋት እየታየ ነው፣ የሚይዝና ሚጨብጠውን ያጣው ዘረኛ የወያኔ አገዛዝ አስከፊ ርምጃ መውሰዱን ቀጥሏል

በትናንትናው እለት ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ያካሄዱትን የጁምዓ ጸሎት ተከትሎ የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ወታደራዊ ሃይሎች አስከፊ ርምጃዎችን እየወሰዱ ሲሆን በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ገዳዩ አገዛዝ እየተከተለ ያለውን አካሄድ በመተቸትና በመቃወም ላይ የሚገኙ መሆኑን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ዘገባ ላይ አመለከተ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በሁሉም የሃገሪቱ ክልሎች ሊባል በሚችል ደረጃ በሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ላይ ያለው ክትትልና ጫና ከመቼውም ጊዜ በላይ የተባባሰ ሲሆን በተለይም፣ በሀረር ግጭቱ ከፍቶ አንድ ከ10 እስከ 12 ዓመት የሚገመት እድሜ ያለው ወጣት መገደሉ ታውቋል። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ሃረር ውስጥ ሙስሊሞች በ4ኛ መስጊድ ተገኝተው ስግደታቸውን ካደረሱ በሁዋላ በሰላም ወደ ቤታቸው እየተመለሱ ባሉበት ወቅት የወያኔ የፌደራል ፖሊስ አባላት የተወሰኑ ወጣቶችን ለማሰር በመፈለጋቸውና ከዚህም ጋር ተያይዞ ሙስሊሞቹ አላግባብ ወጣቶቹን ማሰር አትችሉም በማለታቸው ግጭቱ ሊነሳ ችሏል።

ህዝብ ለሚያቀርበው ሰላማዊና የመብት ጥያቄ ጥይትና ድብደባን ምላሽ በማድረግ የሚታወቁት የዘረኛው አገዛዝ ፖሊሶች (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ

## የሃይለማሪያም ደሳለኝ የፓርላማ ውሎ አውዛጋቢና በሃገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎችም ያጣጣሉት እንደነበር ታወቀ

ወያኔዉ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለ ማሪያም ደሳለኝ ባለፈዉ ማክሰኞ ታህሳስ 23 ቀን 2005 ዓም አሻንጉሊት ፓርላማዉ ዉስጥ ተገኝቶ ከፓርላማዉ አባላት የቀረበለትን ጥየቄዎች ሲመልስ ብዙ ግራ የሚያጋቡና አወዛጋቢ መልሶች መስጠቱንና በምርጫ ዙሪያ የሰጠውን መልስ መሰረታዊ የሚባሉት የፖለቲካ መብቶች ካልተሟሉ በምርጫው አንሳተፍም በማለት አቋም የያዙት በሃገር ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ያሉት 33 ተቃዋሚ ፓርቲዎች ማጣጣላቸውን የዕለቱን የፓርላማ ዉሎ የተከታተለው ዘጋቢያችን በላከልን ዜና ገለጸ።

በያዝነዉ ወር አጋማሽ ላይ በኤርትራ ጉዳይ ከአልጀዚራ ቴሌቪዥን ጋር ባደረገዉ ቃለምልልስ ላይ በሰጣቸዉ የመላምት መልሶች ከፍተኛ ትችት የደረሰበት ሀይለማርያም ደሳለኝ ባለፈዉ ማክሰኞ በእነዚሁ በተተቸባቸዉ ጉዳዮች ላይ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ማብራሪያ ሲሰጥ ዉሏል። በተለይ ከኤርትራ መንግስት ጋር ለመደራደር አስመራን ጨምሮ ዬትም ቦታ ለመሄድ ፈቃደኛች ነን ብሎ የተናገረዉን ንግግር በተመለከተ የቀረበለትን ጥያቄ ሲመልስ አስመራ እሄዳለሁ ያልኩት በየትኛውም ቦታ እንደራደራለን የሚለውን የመንግስት አቋም አጽንኦት ለመስጠት ነዉ ሲል ተናግሯል።

ወያኔዎች እንደ ግል ቤታቸዉ በሚቆጣጠሩት የኢትዮጵያ አሻንጉሊት ፓርላማ ዉስጥ ብቸኛው የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካይ የሆኑት አቶ ግርማ ሰይፉ "ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አስመራ ድረስ በመሄድ ከኤርትራ ጋር ለመደራደር እንደሚፈልጉ ከገለጹ፣ ለእኛ ለተቃዋሚዎችም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለመነጋገር ቢሮውን ክፍት ያድርጉልን" የሚል ጥያቄ ለሀይለማርያም ደሳለኝ ሲያቀርቡ አብዛኛዉን ግዜዉን በሳቅና በቧልት የሚያጠፋዉ ፓርላማ እንደ ተለመደዉ ቢስቅም ሀይለማሪያም ደሳለኝ ግን ለዚህ የህዝብ ጥያቄ ተገቢዉን ምላሽ ሳይሰጥ አልፏል።

ከዚህ በተጨማሪ በቅርቡ የተሾሙትን ሁለት ምክትል ጠ/ሚኒስትሮች በተመለከተ ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ሲሰጥ ሁለቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች ህጋዊ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ሳይሆኑ በጠቅላይ ሚኒስትርነት ማእረግ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው የሚሰሩ ናቸው በማለት አገሪቱ ያላት አንድ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ብቻ መሆኑንና እሱም ደመቀ መኮንን መሆኑን ተናግሯል። ቀድሞዉንም ቢሆን ሁለት ምክትል ጠ/ሚኒስትሮች (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘራፊው የወያኔ አገዛዝ በአዲስ ህግ የዜጎችን ንብረት ለመውረስ እየተጣደፈ መሆኑ ተዘገበ

በፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ተረቅቆ በሚኒስትሮች ም/ቤት ጸድቆ ባለፈው ሀሙስ ለፓርላማ የቀረበው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተዘጋጀው አዋጅ ማሻሻያ ረቂቅ በአጣዳፊ ሁኔታ ባለፈው ሰኞ ለህዝብ ውይይት መቅረቡ እየተተቸ ነው ሲል የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ።

እንደ ኢሳት ዘገባ ፓርላማው ረቂቅ ሕጉን ለዝርዝር ዕይታ ለህግ፣ለፍትህና አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ከመራው በኋላ ኮሚቴው ሰኞ ታህሳስ 22 ቀን 2005 ዓ.ም በረቂቁ ላይ የሚመለከታቸው ወገኖች ተገኝተው አስተያየት እንዲሰጡበት ባስተላለፈው ጥሪ መሰረት ውይይቱ ተካሂዷል::

ቋሚ ኮሚቴው ረቂቅ ሕጉ በተመራለት አንድ ቀን ጊዜ ውስጥ ተወያይቶ ሕጉን ለሕዝብ ውይይት ያቀረበበት ፍጥነት ያልተለመደና ጥድፊያ የታየበት መሆኑን አንድ የህግ ባለሙያ መጠቆማቸውን የዘገበው ኢሳት፣ ምናልባትም የዚህን ሕግ ማሻሻያ ተከትሎ ክስ የሚቀርብባቸው ሰዎች ሳይኖሩ እንደማይቀርና ሕጉ በዚህ ፍጥነት መሰረት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለም/ቤቱ ቀርቦ እንደሚጸድቅ ግምታቸውን አስቀምጠዋል ብሏል::

ዘረኛውና አፋኙ የወያኔ አገዛዝ በአሁኑ ጊዜ በፖለቲካው መስክ የሚቃወሙትን ሁሉ በሽብር ክስ እየከሰሰ ዘብጥያ በማውረድና ንብረታቸውን በመውረስ ላይ እንደሚገኝ በስፋት የሚታወቅ ሲሆን በቅርቡ የጋዜጠኛ እስክንድር ነጋና አንዱአለም አራጌ ንብረት እንዲወረስ አቃቢ ህግ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረቡ ይታወሳል። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየው የውስጥ ተቃውሞ እያየለ መምጣት፣ በውጭ የሚገኙ በተለይም የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ ድርጅቶች በአንድነት እየተንቀሳቀሱ መምጣታቸው ገዢውን ሀይል እያስጨነቀ መምጣቱ ህጎችን ለማርቀቅ ምክንያት ሳይሆን እንዳልቀረ የኢሳት የአዲስ አበባ ዘጋቢ መግለጹ ታውቋል።

## "የኑ እና እዩኝ" ኑዛዚያዊ የወያኔ ጥሪ

የህዝብ ድጋፍ የሌለው የመከላከያ ሠራዊት በየትኛውም አለም ቢሆን ለድል የበቃበት ጊዜ አናሳ ነው። ወያኔዎች ሰሞኑን ከእየአቀጣጫው የተፈጠረባቸውን ውጥረት ለማላላትና ለማስተንፈስ ይረዱኛል ያሏቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች "የኑ እና እዩኝ ኑዛዚያዊ ጥሪ" እያቀረቡ ነው።

እርግጥ ነው ሰራዊቱ በቡሬ ግንባር በመሪዎቹ አድሎአዊ ዘረኛ አስተዳደር ተማሮ እርስ በእርሱ በመታኮስ፤ የበርካታ የሰራዊት አባላት ሂዎት ሲቀጠፍ አይተናል፣ ሰምተናልም፤ ምንአልባት የእነ በረከት የቴሌቪዝን ካሜራ ይኼኛውን አላየው ይሆናል።

ሰራዊቱ ዛሬ በዘር መድሎ እየታሸ፣ ዘረኝነት ለስራ እድገትና ሹመት መመዘኛ በሆነበት፣ ስብእናው፣ ማንነቱ በህወሃት ካድሬዎች ተደፍሮ፣ ሙያው ተዋርዶ እና እርስበርስ ተከፋፍሎ ቀንን እየቆጠረ ባለበት ጊዜ፤ ይህንን ሰራዊት ኢትዮጵያዊ ውክልና ያለው አስመስለው፤ በክፉ ቀን ደራሽ አድረገው መቁጠራቸው ሞኝነት ነው።

ወያኔዎች መራራውን እውነት መራራም ቢሆን፤ በግልጽ የሚታይን፣ ያለውን እውነትና ነባራዊ ሁኔታ እስከመቼ በመካድ ራሳቸውን ሲያታልሉ ይኖራሉ? ሰራዊቱ በአሁኑ ሰአት በየግንባሩ እየከዳ ወደጎረቤት ሀገሮች በመሰደድ የተቃዋሚ ሃይሎችን እየተቀላቀለ ነው። ይህን የመከፋፈልና የመፍረስ ሃቅ ለመደበቅ የተቀነባበረ ትርኢት እናሳያችሁ ሲሉ ራሳቸውን ያታልላሉ።

በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ ለዘረኛ መሪዎች የህብት ማካበቻና የስልጣን እድሜ ማራዘሚያ ውድ ህይወቱን እንደ አልባሌ ነገር በሶማሊያ አደባባዮች እንደተፈጸመበት ሴራ ህይወቱን የሚገብርበት ቅንጣት ያህል ስሜት፣ ሁኔታ አሁን አይኖርም። በተለይም አበው የሰጡንን የታሪክ ማንነታችንንና ሃውልቶቻችንን በማፍረስ፣ አንድነታችንን በማናጋት ለበታተነን እና የአንድን ዘር የበላይነት መሰረት ላደረገ ስርአት፤ ሰራዊቱ ክቶ ክቡር የሆነ ህይወቱን አይለግስም።

ሰራዊቱ ከህዝብ አብራክ የወጣ ለህዝብ በህዝብ የሆነ እንጅ በአሁኑ ዘመን በገዛ ወገኑ ላይ ጥይት የሚያርከፈክፍበት ጊዜ ያለፈበት ለመሆኑ ከአረቡ አለም የጸደይ አቢዮት በተለይም ከግብጹ ህዝባዊ አቢዮት የህዝብ አሸናፊነት፣ ከመከላከያው ጠባቂነት ብዙ ትምህርት የቀሰመ ሠራዊት ነዉ።

እንግዲህ ይህን በዘርና በማንነቱ ከፋፍለው የያዙትን ሰራዊት፣ የእነሱን የከፋፍለህ ግዛ ጥቅም ያስከብርላቸው ዘንድ እየተመኙ ነገርግን ለፍርሃታቸው መደበቂያ አርቲስት ተብዩዎቹን በመጥራት "ኑ ጉልበታችንን እዩና ለህዝብ ንገሩ እኛ ብንናገር የሚሰማን የለም" ሲሉ መማጸናቸውን በቲቪ መስኮታቸው አይተናል። በርግጥ ነው አርቲስቶች የተከበረ ሙያቸውን ለዘር የፖለቲካ ስርአት፣ ህዝባዊ ውክልና ለሌለው አምባገነናዊ አገዛዝ መጠቀሚያ ማድረጋቸው በታሪክ ተጠያቂ ያስደርጋቸዋል።

ሰራዊቱ ሁሉም ዜጎች በእኩልነት የሚኖሩባት፣ አንድነቷ የተከበረባት፣ እውነተኛ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመስረት በሚደረገው ማናቸውም የህዝብ ትግል ከህዝብ ጎን በመቆም የአበውን የጀግንነት አርአያ በመከተል ለአምባገነኖች የስልጣን እድሜ ማራዘሚያና በደሙ ውስኪ ከሚራጩበት ለወያኔ አዛዦች መጠቀሚያ ከመሆን እምቢ ሊል የግድ ይላል። ከህዝብ አብራክ የወጣ የሀገር ልጅ ለሀገር አንድነት ህልውና፣ ለነጻነት ጮራ ትግል እንቅፋት መሆን የለበትም።

ሁሌም ህዝብ አሸናፊ ነው፤ ሙባረክ በአለም አለ የሚባል የጦር ሰራዊትና የቴክኖሎጅ ብዛት የነበረው አምባገነን መሪ ነበር፤ ጋዳፊ የመከላከያ ጡንቻቸውን በቴሌቪዥን መስኮቱ ደጋግመው ለአለም ሲያሳዩ ሲኮፈሱ ነበር፤ ከቶ የአንዱም የሰራዊት ሃይል የህዝብ ቁጣ ማእበልን ሊገታው፣ ሊያቆመው አልተቻላቸውም። ታዲያ የኛዎቹ ትንሽዬ አምባገነን ዘረኛ መሪዎች ምን ሸቷቸው ይሆን የሰራዊት ህብረ-ትርኢት ማሳየት የጀመሩት?

ህወሃት ሁሉን እንደሚያውቅ እና ጥንካሬውን በአዋጅ እንዲናገሩለት በመረጣቸው እንደራሴዎች ሲያስነግር፣ ነገር ግን በአንጻሩ ባዶነቱንና የድንጋጤው መጠኑ ማየሉን ለህዝብ እያሳየ መሆኑን ልብ ያለው አልመሰለንም፤ ታዲያ የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍርሃት አረንቋ በመውጣት የአየሩ ትርኢት ሳያስደነግጠው ትንሽም ትልቅም ቢሆን በራስ አነሳሽነት በየአካባቢው ተደራጅቶ ትግሉን በማገዝ ወያኔን በማስገደድ ወይም የማስወገድና የማፋፋም ሚና መጫዎት ይኖርብናል።

ሰራዊቱ የህዝብ ነጻነትና መብት ሲጠበቅ፤ የእርሱም የነጻነትና ዲሞክራሲያዊ እኩልነቱ እንደሚጠበቅ ተረድቶ ህዝባዊ የነጻነት ትግል ጎራን መቀላቀል ብልህነት ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ኢትዮቴሌኮም የወያኔ ዘረኝነት ፖሊስ መንጸባረቂያ መሆኑን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሚገባ እንደሚያዉቀዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያን ቴሌኮሚኒኬሺን ተቋም ከኋላ ቀርነት ለማላቀቅ በሚል ሰበብ የኮርፖሬሺኑን የማኔጅመንት ዘርፍ ለፈረንሳይ ኩባኒያ መስጠቱ የሚታወስ ነዉ። ወያኔ እንደሚለዉ የኢትዮቴሌኮም ማነጅመንት ለፈረንሳዩ ኩባኒያ የተሰጠዉ የኮርፖሬ ሽኑን አቅም ለማሳደግ ቢሆን ኖሮ መልካም ነበር፤ ነገር ግን ወያኔ የሚናገረዉና የሚሰራዉ ስራ የተለያየ በመሆኑ ዛሬ ወያኔ ኢትዮቴሌኮም በየዘርፉ የረጅም ግዜ ልምድ ያላቸዉን ባለሙያዎች አባርሮ ታማኝ የህወሀት ታጋዮችን በመተካት ኮርፖሬሺኑን የለየለት የስለላ ተቋም አድርጎታል። ስለሆነም ዛሬ ብዙ የአፍርካ አገሮች ትልቅ ግስጋሴ ያደረጉበትና የዜጎቻቸዉን ህይወት የለወጡበት ዘርፍ ኢትዮጵያ ዉስጥ ዜጎችን እየሰለለ አገረን የመረጃ ጨለማ ዉስጥ የከተተ ተቋም ሆኗል።

ባላፉት ሁለት አመታት የኢትዮቴሌኮም ማነጅመንት ኤን አንድና ኤን ሁለት በሚባሉ ሁለት ከፍተኛ የአስተዳደር እርከኖች ተከፍሎ በሁለቱም ከፍተኛ የአመራር እርከኖች ዉስጥ የሰዉ ኃይል ተመድቧል። ይህ በከፍተኛ ማነጅመንት ደረጃ የተመደበዉ የሰዉ ኃይል ኢትዮጵያዉያንንና የፈረንሳይ ዜጎችን የሚያጠቃልል ነዉ። በኤን አንድና በኤን ሁለት የማነጅመንት ደረጃ የስራ ድርሻ የተሰጣቸዉ ኢትዮአጵያዉያን በቁጥር 54 ሲሆኑ ከዚህ ዉስጥ 46.3 በመቶ ወይም ሃያ አምስቱ የትግራይ ተወላጆች ናቸዉ። በዚህ ከፍተኛ የማነጅመንት እርከን ዉስጥ የኦሮሞ፤ የአማራና የተቀሩት ስድስት ክልሎች ድርሻ በቅደም ተከተል 18.5 በመቶ፤ 29.6 በመቶና 5.6 በመቶ ብቻ ነዉ። ከሁለቱ የማነጅመንት እርከኖች ዉስጥ ኤን አንድ የሚባለዉ ከፍተኛዉ ሲሆን በዚህ እርከን ዉስጥ ሰምንት የትግራይ ተወላጆች ሲኖሩ የአማራና የኦሮሞ ተወላጆች እያንዳንዳቸዉ ሁለት ቦታ የያዙ ሲሆን በዚህ ከፍተኛ የአመራር እርከን ዉስጥ ከተቀሩት ስድስት ክልሎች የተመደበ አንድም ሰዉ የለም።

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ከእያንዳንዱ 3.3 ሚሊዮን የኦሮሞ ተወላጅ ዉስጥ በኢትዮ ቴሌኮም ከፍተኛ አመራር ቦታ የተሰጠዉ አንድ የኦሮሞ ተወላጅ ብቻ ሲሆን ትግራይን ስንመለከት ግን ከእያንዳንዱ 194 ሺ የትግራይ ተወላጅ ዉስጥ ቢያንስ አንድ ሰዉ በኢትዮ ቴሌኮም ከፍተኛ አመራር ቦታ ላይ ተቀምጧል። ይህ የስራ አመዳደብ የትምህርት ችሎታንና ልምድን ተከትሎ የተሰራ ነዉ ቢባል እንኳን የላቀ የትምህርት ደረጃና የስራ ልምድ ያለቸዉ የኦሮሞ ተወላጆች ቁጥር ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃና የስራ ልምድ ካላቸዉ የትግራይ ተወላጆች ቁጥር በአስር እጥፍ መብለጡ ምንም ጥርጥር የለዉም። ሌላም መራራ ሀቅ አለ። 66.2 በመቶ የሚሆነዉን የኢትዮጵያ ህዝብ ከሚያቅፉት ከኦሮሚያና ከአማራ ክልል N1 በሚባለዉ ከፍተኛ የአመራር እርከን ዉስጥ በአመራር ቦታ የተቀመጡ ዜጎች ብዛት አራት ብቻ ነዉ (ሁለት ከኦሮሚያ ሁለት ከአማራ)። ከጠቅላላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ዉስጥ 5.4 በመቶዉ ብቻ ከሚኖርበት ከትግራይ ክልል ግን ስምንት ሰዎች ኤን አንድ በሚባለዉ ከፍተኛ የአመራር ቦታ ላይ ተቀምጠዋል።

በኢትዮ ቴሌኮም ከፍተኛ አመራር ቦታ ላይ ከተቀሩት ስድስት የአገሪቱ ክልሎች የመጡትን ሰዎች ስንመለከት የሚታየዉ ስዕል እጅግ በጣም የሚያሳዝንና ወያኔ የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት እያለ ከሚሰብከዉ ስብከት ጋር የሚጋጭ ነዉ። በ2012 ከኦሮሚያ፤ ከአማራና ከትግራይ ክልል ዉጭ በተቀሩት ስድስት ክልሎች ዉስጥ የሚኖረዉ ህዝብ 25,627,349 እንደሚሆን ይገመታል። ከዚህ ህዝብ ዉስጥ በኢትዮ ቴሌኮም ከፍተኛ አመራር ቦታ ላይ የመቀመጥ እድል ያገኙት 0.000012 በመቶ ብቻ ወይም ከእያንዳንዱ 8.5 ሚሊዮን ህዝብ አንዱ ብቻ ነዉ። እንግዲህ ይህንን ነዉ ወያኔ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች እኩልነታቸዉን ተጎናጽፈዋል እያለ የሚናገረዉ።

የግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከዚህ ቀደም ወያኔ "የኢትዮጵያ መከላከያ" ጦር እያለ የሚጠራዉን ሠራዊት ምን ያክል የኔ በሚላቸዉ የህወሀት ሰዎች ብቻ እንደሚቀጣጠር የሚያሳይ መግለጫ በመረጃ አስደግፎ ለህዝብ ማቅረቡ የሚታወስ ነዉ። አሁንም ወያኔ ኢትዮቴሌኮምን ምን ያክል የራሱ የቤት ዉስጥ እቃዉ እንዳደረገዉ የሚያሳየዉን በጽሁፍና በአኃዝ የተፈገፈ መረጃ በዛሬዉ እለት ለህዝብ ይፋ የሚያደርግ መሆኑን እየገለጸ ከአሁን በኋላም የወያኔን ዘረኝነትና ህግወጥነት የሚያጋልጡ ስራዎችን በተከታታይ እየሰራ ለህዝብ የሚያቀርብ መሆኑን ይገልጻል።

# ለነፃነቱ የቆረጠን ህዝብ የሚያቆመዉ ምንም አይነት ምድራዊ ኃይል የለም

ከጥንቶቹ ባቢሎናዉያን፤ ሮማዉያንና ግሪኮች አስከ መካከለኛዉ ዘመን እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ከዚያም በቅርቡ እንዳየናቸዉ የቱኒዝያ፤ የግብፅና የሊቢያ ህዝብ ወይም ዛሬም ትንቅንቅ ላይ የሚገኘዉ የሦሪያ ህዝብ ታሪክ የሚነግረን አንድ ብቸኛ ሀቅ ቢኖር አምባገነኖች ያሻቸዉን ያክል ሀይል ቢገነቡ ወይም ምድር ላይ አለ የሚባለዉን የጦር መሳሪያ ሁሉ ቢታጠቁ የህዝብን መብት አስካላከበሩና ህዝብ አስካልወደዳቸዉ ድረስ እንደ ዲንጋይ ካብ ተንደዉ መጨፍለቃቸዉ አይቀርም። አምባገነኖች ህዝብን ማስጨነቅ፤ ማሰር፤ መደብደብና መግደል ይችሉ ይሆናል ሆኖም የአምባገነኖችን የበላይነት ተሸክሞ የኖረን ህብረተሰብ ታሪክ መዝግቦት አያዉቅም፤ እናት አገራችን ኢትዮጵያም የዚህ አይነት ቆሻሻ ታሪክ መጀመሪያ አትሆንም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ደርግን ለ17 አመት ወያኔን ደግሞ ላለፉት ሃያ አንድ አመታት ተሸክሞ ኖሯልና ስለ ስላምባገነኖች ሊነገረዉ የሚገባ ህዝብ አይደለም። ደርግ በአፍሪካ አህጉር ትልቁን ጦር ገንብቶ ከሚቃወሙህ ጋር በሠላም ተደራደር ሲባል “ እንደ ዉኃ የሚያጥለቀልቅ ኃይል አለኝ” ብሎ ሲኮፈስ ለእግሩ ጫማ በሌላዉና በሚገባ ባልሰለጠነ ኃይል ተጥለቅልቆ እንደ በረሃ ዉስጥ ዉኃ ተንኖ ጠፍቷል። የአምባገነኖች መምጫቸዉ እንጂ መጥፊያቸዉ አይለያይምና የዛሬዎቹም ባለሳምንቶች እንደ መንግስቱ ሀይለ ማሪያም፤ እንደ ፒኖቼ፤ አንደ ሙባረክና እንደ ጋዳፊ አንድ ቀን የታሪክ አተላ ሆነዉ መደፋታቸዉ አይቀርም፤ ያ “አንድ ቀን” ደግሞ ዛሬ ከምን ግዜም በላይ አጥራቸዉ ዉስጥ ዘልቆ ገብቶ ቤታቸዉን እያንኳኳ ነዉ። የወያኔ አምባገነኖች ያላቸዉ ብቸኛ አማራጭ አንደ ሙባረክ በግዜ እጅ ሰጥተዉ የበደሉትን ህዝብ ማረን ብሎ መለመን አለዚያም እንደ ጋዳፊ ቱቦ ለቱቦ መንተት ነዉ። ከዚህ ዉጭ ግን ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ህዝብን ለማስፈራራትና እኛን የሚደፍር ወዮለት የሚል ደካማ መልዕክት ለማስተላለፍ ከሰሞኑ የጀመሩትን የሞኝ ድራማ የሚያይላቸዉ የለምና ካሁኑ ሳይጀምሩት ቢያቆሙ ለእነሱም ቢሆን ይበጃቸዋል።

“እግዚአብሔር ሊያጠፋዉ የፈለገዉን መጀመሪያ የሳብደዋል” ይላሉ አበዉ ሲተርቱ። ዘንድሮ በተለይ ከሰሞኑ ወያኔ የሚያሳየን አዲስ ጸባይ ከላይ ከጠቀስነዉ የአበዉ ተረት ብዙ የራቀ አይደለም። ወያኔ መጥፊያዉ ስለደረሰ እያበደ ነዉ። አዎ! ወያኔ መጥፊያዉ እንደደረሰ በሚገባ ተረድቶ በአጥፍቼ ልጥፋ አባዜ ተለክፎ እያበደ ነዉ። ጨዋዉ፤ አስተዋዩና ይቅር ባዩ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን አሁንም የይቅርታ እጁን እንደዘረጋ ነዉ፤ ወያኔ ማበዱን አምኖ ጤንነት ከተመኘ ያ “ዬኔ ነዉ” የሚለዉ የገጠሩ ህዝብ አብሾ ሊሰጠዉ ከተሜዉ ደግሞ አማኑኤል ሊወስደዉ ሙሉ ፈቃደኛ ነዉ። አዉቆ አበዱ ወያኔ ይህንን አማራጭ አሻፈረኝ ብሎ ምርጫዉ በእብደት መቀጠል ከሆን ግን የኢትዮጵያ ህዝብ ይቅር ባይ ነዉ አንጂ አዉቆ አበድ አስተናጋጅ ስላልሆነ በቅርቡ የአረቡ አለም አዉቆ አበዶችን ባስተናገደበት መንገድ ወያኔም ይስተናገዳል ። አዚህ ላይ ካለምንም ጥርጥር ወያኔን አስረግጠን ልንነግረዉ የምንፈለገዉ አንድ ቁም ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔን እንደ ሙባረክ ወይም እንደ ጋዳፊ ከማስተናገድ የሚያቆመዉ ምንም አይነት ምድራዊ ሀይል እንደሌለ ነዉ።

ከሰሞኑ ወያኔ አንዳንድ ሰብዓዊነት የጎደላቸዉንና የወገን ሰቀቃና ጩኸት የማይሰማቸዉን ግዑዝ የህብረተሰብ ክፍሎች ሰብስቦ ዘረኝነትን መሠረት አድርጊ የተገነባዉን የደህንነት፤የፖሊስ፤የአየር ሀይልና የምድር ጦር ተቋሞቹን በማስጎብኘት ከወያኔ ጋር የሞት የሽረት ትግል ዉስጥ የገባዉን የኢትዮጵያ ህዝብ ለማስፈራራትና ከኔ ዉጭ የሚያዋጣህ ምንም ነገር የለም የሚል የፈሪ መልዕክት ለማስተላለፍ ዉር ዉር እያሉ ይገኛሉ። የእነዚህ ደካማዎች መልዕክት ደግሞ ግልጽ ነዉ። የፈረጠመ ጡንቻ አለኝ፤ በከተማ ዉስጥ ከፈለጋችሁኝ ጠንካራ የፖሊስና የድህንነት ሀይል አለኝ፤ በሰማይ ካሰባችሁኝ ሰማዩ ዬኔ ብቻ ነዉ፤ በድንበር በኩል ከመጣችሁም ጠንካራ የምድር ጦር አለኝ የሚል ነዉ። እዚህ ላይ አንድ ልብ ልንለዉ የሚገባን ነገር ቢኖር ወያኔ ምንም ነገር ነኝ ወይም አይደለሁም ቢል እንኳን የሚያምነዉ ቀርቶ ጆሮ ሰጥቶት የሚሰማዉ ኢትዮጵያዊ እንደሌለ ያዉቃል። ለዚህም ነዉ ምድረ ሆዳም ምስለኔዎችን ሰብስቦ “ወያኔ አይቻልምና” አርፋችሁ ተገዙ የሚል መልዕክት ለኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያስተላልፉ ሆዳቸዉን ሞልቶላቸዉ አፋቸዉን እንዲከፍቱ ትዕዛዝ የሰጣቸዉ። እዚህ ላይ አጅግ በጣም የሚገርመዉና የሚያሳዝነዉ ዛሬ የወያኔን ትዕዛዝ ተቀብለዉ ለመብቱና ለነጻነቱ ለሚታገለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔን ጥንካሬና አለመሸነፍ የሚነግሩን ደካማ ፍጥረቶች ደርግን የመሰለ እጅግ በጣም ጠንካራ ሀይል “ነጠላ ጫማና” “ቁምጣ ሱሪ” በለበሰ እንዲሁም በብዛቱና በትጥቁ ከደርግ እጅግ በጣም ባነሰ ሀይል ሲደመሰስ በአይናቸዉ ብሌን ተመልክተዉ “ጉድ” ያሉ ሰዎች ናቸዉ። ችግሩ እነዚህ ደካሞች “ያሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ” የሚሉትን ተረት ስለማያዉቁ ነዉ እንጂ ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ “ጉድ” የሚለዉ የእነሱን ክህደትና የሞራል ደከማነት እየተመለከተ ነዉ። ወያኔም ሆነ እነዚህ ደካማ ሰዎች የሚገባቸዉ ከሆነ ዛሬ ወያኔ የሚዋጋዉ እንደሱ ከተደራጀና ከታጠቀ ሀይል ጋር ሳይሆን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ነዉ። ከህብ ጋር ተዋግቶ ያሸነፈ ሀይል ደግሞ አልነበረም፤የለም አይኖርምም።

ለመሆኑ ወያኔ ስልጣን ከያዘ ከሃያ አንድ አመት በኋላ ዛሬ “የመከላከያ ቀን” ተብሎ የሚታሰብ ቀን ፈጥሮ ለማክበርና ይህንኑ በዐል አስታክኮ ከህዝብ የመለመለዉን ሠራዊትና የታጠቀዉን መሳሪያ አይነትና ብዛት ለኢትዮጵያ ህዝብ ለማሳየት የፈለገዉ ለምንድነዉ? የወያኔ መሪዎች ከዚህ ቀደም ባንዲራችንን ጨርቅ ማለታቸዉ ብቻ ሳይሆን በረህ ዉስጥ እያሉ ዕቃ ለመጠቅለል ይጠቀሙበት ነበር። ዛሬ ያንን ኃጢያታቸዉን ለመሸፈን የባንዲራ ቀን እያሉ ማክበር ጀምረዋል። የህወሀት መሪዎቸችና የቅርብ ዘመዶቻቸዉ የኢትዮጵያን ኤኮኖሚ፤ ፖለቲካና የጦር ኃይሎች ሙሉ ለሙሉ እየተቆጣጠሩ ኢትዮጵያ ዉስጥ የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት ፈጠርን እያሉ ላለፉት ስምንት አመታት የፌዴራሊዚም ቀን እያሉ ህዝብን እያታለሉ ኖረዋል። አሁን ደግሞ ያ ሁሉ አልበቃ ብሏቸዉ የመጀመሪየዉን የመከላከያ ቀን ለማክበር ጉድ ጉዱን ተያይዘዉታል። ለመሆኑ ይህ ሁሉ የበዐል ጋጋታ ለምን አስፈለገ?

አንዳንዴ ፈርንጆች ስለ አንድ ዕቃ ጥሩነት ሲናገሩ “ጥሩ ዕቃ” ማስታወቂያ አያስፈልገዉም ይላሉ። ለመሆኑ ወያኔ “የባንዲራ ቀን”፤ “የፌዴራሊዝም ቀን” አሁን ደግሞ “የመከላከያ ቀን” እያለ የሚያስተዋዉቀን የቀኖቹን መልካምነት ነዉ . . . . . ወይስ ነገሩ “መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ” ነዉ? ባንዲራ “ጨርቅ ነዉ” ተብሎ እንደ ተራ ጨርቅ ዕቃ የሚጠቀለልበት ከሆነ ኢትዮጵያ ዉስጥ የጨርቁ ብዛት ዬትየለሌ ነዉ፤ ታድያ “ጨርቅ ነዉ” ተብሎ የተናቀ ባንዲራ ለምን የባንዲራ ቀን አስፈለገዉ?

ጉዳዩ እንደዚህ ነዉ። ወያኔ ባንዲራ አለ፤ ፌዴራሊዝም አለ፤ ወይም ህገ መንግስት አለ ሁሉም እሱን አስቀጠቀሙት ድረስ ብቻ ነዉ። እነዚህ ለአገርና ለህዝብ እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆኑ እሴቶች አገርና ህዝብን ጠቀሙ አልጠቀሙ ወያኔ ጉዳዩ አይደለም። የወያኔ ጉዳይ እነዚህን እሴቶች እየተጠቀመ ህዝብን አታልሎ የስልጣን ዘመኑን ማራዘም ነዉ። ዛሬም “የመከላከያ ቀን” ተብሎ በአል ለማክበር የሚደረገዉ ሽር ጉድ በአሉን ተጠቅሞ ወያኔ ላይ የተነጣጠረዉን የህዝባዊ ቁጣና አመጽ አቅጣጫ ለማስቀየር የሚደርግ ሩጫ ነዉ እንጂ ለወያኔ ጥቅም ብቻ ከቆመዉ ጥቅት የአግአዚ ሠራዊት ዉጭ በዘረኝነት የሚሰቃየዉ ሌላዉ የኢትዮጵያ ሠራዊት በአል ናፍቆት አይደለም።

ኢትዮጵያ ዉስጥ ዘረኝነት በከፋ መልኩ እራሱን ከገለጸባቸዉ የተለያዩ ተቋሞች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ የመከላከያ ሠራዊት ነዉ። ዛሬ አብዛኛዉ የኢትዮጵያ ሠራዊት አባላት የሚፈልጉት ወይ ዘረኝነት አለዚያም የዘረኝነቱ አባት ወያኔ ከአትዮጵያ ምድር ተጠራርጎ እንዲጠፋ ነዉ እንጂ ምንም ትርጉም የሌለዉ የመከላከያ ቀን ሲከበር መመልከት አይደለም። ወያኔና ዘረኝነት ደግሞ በስም እንጂ በቅርጽም ሆነ በይዘት ስለማይለያዩ ከኢትዮጵያ ዉስጥ ወያኔ ከተነቀለ ዘረኝነትም በራሱ አይቆምምና አንዱ ሲነቀል ሌላዉም አብሮት መነቀሉ አይቀርም። እንግዲህ ወያኔ ዛሬ “የመከላከያ ቀን” አከብራለሁ እያለ ሽር ጉድ የሚለዉ በአንድ በኩል በዘረኝነት አለንጋ የሚገረፈዉን ሠራዊት ለመደለል በሌላ በሌላ በኩል ደግሞ ሞኙ ደርግ እንዳለዉ “እንደ ዉኃ” የሚያጠለቀልቅ ኃይለ አለኝ እያለ ህዝብን ለማስፈራራትና ለመብቱና ለነፃነቱ እንዳይታገል ለማድረግ ነዉ።

ሰዉ በላዉ ደርግ ከ400 ሺ በላይ ጠንካራና የረጂም ዘመን የዉግያ ልምድ የነበረዉ ጦር ነበረዉ፤ የደርግ ጦር ከማንኛዉም የጥቁር አፍሪካ አገር በላይ የታጠቀ ጦር ነበር፤ በደርግ ዘመን የነበረዉ የኢትዮጵያ አየር ኃይል በአፍሪካ ዉስጥ ተወዳዳሪ አልነበረዉም፤ ዛሬ ወያኔ የመከላከያ ኢንጂኔሪንግ ገነባሁ ብሎ የሚኩራራበት ትልቁ ወታደራዊ እንጂኔሪንግ ተቋምም ቢሆን የዚሁ የደርግ ዉጤት ነዉ እንጂ ወያኔ ሊነግረን እንደሚፈልገዉ እሱ የሰራዉ ስራ አይደለም። እንግዲህ ይታያችሁ ደርግ ይህንን ሁሉ ወታደር፤ ወታደራዊ ተቋምና የመሳሪያ ብዛት ይዞ ነዉ ከሱ በቁጥር እጅግ ባነሰና በሚገባ ባልሰለጠነ ሚሊሺያ ጦር ተሸንፎ የጠፋዉ። ደርግን ለማጥፋት የ17 አመት የትጥቅ ትግል አስፈልጓል። ህዝብ እክ እንትፍ አድርጎ የተፋዉን ወያኔን ለማጥፋት የዚህ ግዜ ሩብም አያስፈልግም።

ከሰሞኑ አዲስ አበባ ዉስጥ እራሳቸዉን “አርቲስቶች” ብለዉ የሰየሙ የጥፋት ተዋንያንና ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በመቀናጀት ሊከይኑት የሚፈልጉት “ የመከላከያ ቀን” ድራማ ልብ ያለዉ ተመልካች አይኖረዉም እንጂ ቢኖረዉ ኖሮ ይህ አርታኢዉም መሪ ተዋንያኑም ጅላጅል የሆኑበት ድራማ የወያኔን ትንሽነትና የአርቲስት ተብዬዎቹን ተላላኪነት በግልጽ የሚያሳይ ድራማ ይሆን ነበር። የሚገርመዉ ይህ “የማይሞከር” ግዙፍ ኃይል ነዉ ተብሎ በድራማ መልክ ለህዝብ እይታ ሊቀርብ የታቀደዉ የመከላከያ ሠራዊት በአሁኑ ሰአት በየግንባሩና በያለበት ቦታ ሁሉ ወያኔን እየከዳ የነፃነት ኀይሎችን እየተቀላቀለ ነው። መቼም ይህ በፈረንጆቹ አዲስ አመት የመጀመሪያ ሁለት ወራት ዉስጥ ሊከበር ሽርጉድ የሚባልለት “የመከላከያ ቀን” በአል ይህን በፍጥነት በመናድ ላይ ያለዉን ጦር ገመና ለመደበቅ ካልሆነ በቀር ሌላ ምንም ፋይዳ ያለዉ አይመስለንም።

እንገዲህ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ይህንን ምስጥ እንደበላዉ አጥር በየቀኑ የሚፈርሰዉን ሰራዊት ነዉ ወያኔና ለዚህ ሰሞን የተከራያቸዉ ጌኛ ፈረሶች አንደ ትልቅና አንደማይበገር ሀይል አድርገዉ አንተን ለማስፈራራት የጅል ድራማ መስራት የጀመሩት። የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ከዚህ ህዝብ አብራክ የወጣዉ የመከላከያ ሠራዊት ግን “ማን ሀይለኛ” “ማን ደካማ” እንደሆነ ጠንቅቀዉ ያዉቃሉ። በተለይ ከኢትዮጵያ ህዝብ አብራክ የወጡ የፖሊስና የመከላከያ ሠራዊት አባላት ወያኔ እነሱኑ ተጠቅሞ እነሱንና እነሱ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በኢትዮጵያ የተለያዩ ከተሞች ከፍተኛ አለመረጋጋት እየታየ

. . . (ከገጽ 3 የዞረ)

በትናንትናው እለትም በተኮሱት ጥይት ህጻኑን ከመግደላቸው በተጨማሪ እናቱንም እንዳቆሰሉዋት የአይን እማኞችን ዋቢ በማድረግ ዘጋቢያችን በላከልን ሪፖርት ገልጿል። በዚሁ በሃረር በተነሳው ግጭት ሌሎች ሶስት ነዋሪዎችም በጽኑ መቁሰላቸውንና በርካታ ወጣቶችም ታፍሰው ወደ እስር ቤት መወሰዳቸውን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጿል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በወልድያ ደግሞ የጸጥታ ሀይሎች በርካታ ሙስሊም ወጣቶችን ይዘው ያሰሩ ሲሆን ወጣቶቹ የታሰሩት በአልበሲጥ መስጊድ ስግደት ካደረጉ በሁዋላና "መሀይም አይመራንም፣ የታሰሩ መሪዎቻችን ይፈቱ"፣ "መንግስት ሊመራ አልቻለም ይወረድ" የሚሉ መፈክሮችን በማሰማታቸው መሆኑን ዘጋቢያችን ወልዲያ የሚገኙ አንዳንድ ሙስሊሞችን በስልክ በማናገርና በማጠናቀር በላከው ዘገባ ገልጿል።

ህዝብን ርስ በርስ ማጋጬት እንደ ስልት አድርጎ የሚጠቀመው የወያኔ አገዛዝ ወልዲያ የሚገኙ በአነስተኛ እና ጥቃቅን የተደራጁ ወጣቶችን በማሰለፍ በሙስሊሞቹ ላይ ጸረ ልማት የሚል ቅስቀሳ ለማካሄድ መሞከሩን፣ ያነጋገራቸው የወልዲያ ነዋሪዎች መናገራቸውን ዘጋቢያችን ገልጿል። በዚሁ በወልድያው ግጭት በርካታ ወጣቶች በፌደራል ፖሊስ መኪኖች እየተጫኑ ወደ እስር ቤት መወሰዳቸውን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አረጋግጧል።

በትናንትናው እለት ታላቁን የአንዋር መስጊድ ጨምሮ በደሴ፣ በአዋሳ፣ በሻሸመኔ እና በአዳማ ( ናዝሬት) ተመሳሳይ የተቃውሞ ድምጾች የተሰሙ ሲሆን ጨፍጫፊው የወያኔ አገዛዝ የሙስሊሞችን ሰላማዊ ጥያቄ ከሽብርተኝነት ጋር እያያዘ ወደ አልሆ አቅጣጫ እየገፋው መምጣቱ ብዙዎችን ያሳሳበ ጉዳይ ሆኗል።

ይህ በንዲህ እንዳለ ከትናንት በስቲያ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተከሰተው ግጭት ቀጥሎ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አሁንም በልዩ ጥበቃ ስር መሆኑን ዘጋቢያችን በላከልን ሪፖርት ገለጸ። እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት ከትናንት ማታ ጀምሮ የደህንነት ሀይሎች በኢህአዴግ ደጋፊ ተማሪዎች እየተመሩ ለግጭቱ መነሳት እና መባባስ ምክንያት ሆነዋል ያሉዋቸውን ተማሪዎች ስም ዝርዝር ማውጣታቸውና የተወሰኑ ተማሪዎች በግዳጅ መታወቂያቸውን ተነጥቀው ወደ አልታወቀ ስፍራ መወሰዳቸው ታውቋል።

ወያኔ ሃያ አንድ አመት ሙሉ ሲቋጥር የከረመዉ የዘርና የጎሳ ችግር አዲስ አበባ የኒቨርሲቲ ዉስጥ ተማሪዎች ጎራ ለይተዉ እንዲደባደቡ ማድረጉን ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና የገለጹ ሲሆን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ ፋኩልቲ ግቢ ዉስጥ በተፈጠረዉ የተማሪዎች ግጭት የኦሮሞና የትግራይ ተማሪዎች ጎራ ለይተዉ መደባደባቸውን፣ የግጭቱ ስፋት ከዩኒቨርሲቲዉ ፖሊስ ቁጥጥር ዉጭ በመሆኑ አድማ በታኝና ግጭት አስወጋጅ የፌዴራል ፖሊሰ ወደ አካባቢዉ በፍጥነት መለኩን ዘጋቢዎቻችን አክለዉ ገልጸዋል። በዚህ ረቡዕ ምሽት ላይ ተጀምሮ ሐሙስ ጧት ላይ እንደገና ባገረሸበት ግጭት ብዙ ተማሪዎች ጉዳት ደርሶቸዉ ወደ ሆስፒታል እንደተወሰዱ ለማወቅ ተችሏል። ግጭቱን በወቅቱ ማብረድ የተሳነዉ የፌዴራል የፖሊስ ተማሪዎችን በካሚዮኖችና በፒክአፕ መኪናዎች እየጫነ ወዳልታወቀ ቦታ ወስዷል። ግጭቱ ወደ ስድስት ኪሎ ግቢ ተዛምቶ ከቁጥጥር ዉጭ ሊሆን ይችላል የሚል ስጋት ያደረባቸዉ የፌዴራል ፖሊስ አባላት ከአራት ኪሎ ወደ ስድስት ኪሎ የሚወስደዉን መንግድ ለሰአታት ዘግተዉት እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። የፌዴራል ፖሊስ የግጭቱን መንስኤ ለመናገር ፈቃደኛ ባይሆንም ከአንዳንድ ተማሪዎች በተገኘዉ መረጃ መሠረት ግጭቱ የተፈጠረዉ በዩኒቨርስቲዉ የሚገኙ የትግራይ ተማሪዎች የኦሮሚያን ተማሪዎች የሚያንቋሽሽ ንግግር አደርገዋል ጽሁፍም በትነዋል በሚል እንደሆነ ተናግረዋል።

በሌላም በኩል ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አለመረጋጋት በስፋት መቀጠሉና እጅግ አስጊ ሁኔታ ላይ እየደረሰ መሆኑ እየተገለጸ ሲሆ በደቡብ ክልል በቤንቺ ማጂ ዞን በቤሮ ሻሻ ወረዳ በሳሊ ቀበሌ በሚገኝ ባህላዊ የወርቅ ማዕድን ማውጫ መንደር በተከሰተው የእርስ በርስ ግጭት ከ 162 ሰዎች በላይ መገደላቸውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘግቧል።

## የሃይለማሪያም ደሳለኝ የፓርላማ ውሎ አውዛጋቢና በሃገር ውስጥ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

መሾም ያስፈለገዉ የኦህዴድን አፍ ለማስዘጋት ስለነበር ሀይለማርያም ደሳለኝ አገሪቱ ያላት አንድ ህጋዊ አንድ ም/ል ጠቅላይ ሚኒስትር ብቻ መሆኑን በግልጽ መናገሩ በህወሀት እና በኦህዴድ ውስጥ ቀደም ብሎ የነበረው የጥላቻና ያለመግባባትና ያለመተማመን ስሜት እንደገና ሊያገረሽበት እንደሚችል አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ።

ሀይለማርያም ደሳለኝ በአገሪቱ ዉስጥ ስለደረሰዉ ከፍተኛ የጤፍ እጥረት ሲያስረዳ በኢትዮጵያ የተፈጠረው የጤፍ እጥረት ጤፍ በልቶ የማያውቀው ህዝብ ጤፍ መብላት በመጀመሩ ነው በማለት ከጌታዉ ከመለስ ዜናዊ የተማረዉን መልስ ሰጥቷል። ከዚህ ቀደም መለስ ዜናዊ የስኳር ዋጋ የተወደደው አርሶ አደሩ ስኳር መብላት በመጀመሩ ነው የሚል የቅጥፈት ጥግግር ማድረጉ ይታወሳል።

በመጨረሻም ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ እስረኛ የለም የሚል አደናጋሪ ንግግር በማድረግ ክርስቲያን በመሆኔ አልዋሽም ሲል የነበረዉ ሀይለ ማሪያም ደሳለኝ ዉሸት ብቻ ሳይሆን ክህደት የሞላበት መልስ በመስጠት የዕለቱን የፓርላማ ዉሎዉን ጨርሶ ወደ ቤተመንግስቱ ሄዷል።

ሃይለማሪያም ደሳለኝ እንደመለስ ዜናዊ "ተቃዋሚዎች በመጪው የአካባቢ ምርጫ የማይሳተፉት ከምርጫው በሁዋላ የሚያስገኘው ጥቅም ስለሌለ ነው" በማለት ለአሻንጉሊቱ ፓርላማ ምክር ቤት አባላት የተናገረውን በሃገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱት ተቃዋሚዎች አጣጥለውታል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መሰረታዊ የሚባሉት የፖለቲካ መብቶች ካልተሟሉ በምርጫው አንሳተፍም በማለት አቋም የያዙት 33 የፖለቲካ ድርጅቶች ሰብሳቢ የሆኑት አቶ አስራት ጣሴ ተቃዋሚዎች በምርጫ የሚሳተፉት ለጥቅም ብለው ሳይሆን ምርጫ የዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ሂደት በመሆኑ ነው ማለታቸውን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቷል። በአዲስ አበባ እና አካባቢ ምርጫ መሳተፍ ጥቅም ከሌለው የትኛው ምርጫ ነው ጥቅም ያለው በማለት የጠየቁት አቶ አስራት በምርጫ 2002 ምርጫ ቦርድ የሰጣቸውን ገንዘብ መልሰው መላካቸውን በምሳሌነት የጠቀሱ ሲሆን በአንጻሩ ሃይለማሪያም ደሳለኝ ደግሞ ተቃዋሚዎች በምርጫው አብረውት ቢሮጡም ባይሮጡም ለውጥ እንደሌለው መናገሩን የደረሰን ዘገባ አመልክቷል።

## ለነፃነቱ የቆረጠን ህዝብ የሚያቆመዉ ምንም አይነት

. . . (ከገጽ 3 የዞረ)

ለመብቱና ለነፃነቱ መከበር የቆሙለትን ህዝብ እንደሚያስር፤ አንደሚደበድብና አንደሚገድል ከተገነዘቡ ቆይቷል።

በአለም ላይ ጥፋት እንዳጠፉ ኖረዉ የእነሱ ቢጤ ከሠራዉ ስህተት ሳይማሩ የሚሞቱ ደነዝ ፍጥረቶች ቢኖሩ አምባገነኖች ብቻ ናቸዉ። አምባገነኖች ከራሳቸዉም ሆነ ሌሎች አምባገነኖች ከሰሯቸዉ ስህተቶች በፍጹም አይማሩም፤ ዛሬ የኢትዮጵያን ህዝብ ያሳዘነዉም የገረመዉም ነገር ቢኖር የአምባገነኖች ደነዝ መሆን አይደለም . . . . . በሚገባ ያዉቃቸዋልና! የኢትዮጵያን ህዝብ ከልብ ያሳዘነዉ ባህሌን፤ ወጌንና ታሪኬን ያለመልሙልኛል ከትዉልድ ወደ ትዉልድም ያስተላልፉልኛል ብሎ እምነቱን የጣለባቸዉ አንዳንድ “አርቲስት” ተብዬዎች የኢትዮጵያን ህዝብ ባህልና ታሪክ ከሚጸየፉ ሰዎች ጋር እጅና ጓንት መሆናቸዉ ነዉ። ከኢትዮጵያ ህዝብ የነፃነትና የእኩልነት ጥማት ጋር ሲወዳደር ወያኔ ከትንሽም ትንሽ ነዉና እንኳን ትልቅነቱን ዛሬ ትንሽነቱንም የሚናገርበት አፍ የለዉም። ኢዚህ ላይ በጣም የሚያሳዝነን ነገር ቢኖር እነዚያ እራሳቸዉን “አርቲስቶች” ብለዉ ወያኔ እንዲጋልብባቸዉ የፈቀዱ ሀይሎች አልገባቸዉም እንጂ ወያኔ ስለራሱ የሚናገርበት አፍ ስለሌለዉ ወይም እየተንተባተበ ቢናገርመ የሚሰማዉ ስለሌለ ነዉ እነሱን የተከራያቸዉ እንጂ እነሱንም ቢሆን ወድዷቸዉ አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ወጣቱ፤ ሠራተኛዉና በወያኔ የዘረኝነት ወጥመድ ተተብትቦ የሚሰቃየዉ የአገር መከላከያ ሠራዊት አባላት ወያኔ የህዝብን የአምጽ፤የእምቢተኝነትና ለነፃነት የመነሳሳት ስሜት ለመስበር የሚወስዳቸዉን አርምጃዎች ሁሉ በመበጣጠስ ለአገር አንድነት፤ ለመብት፤ ለነጻነት፤ ለዲሞክራሲና ለአኩልነት የሚደረገዉን ትግል የመቀላቀል ታሪካዊ፤ ወገናዊና አገራዊ አደራ አለባቸዉ። ወያኔ የቱንም ያክል ትልቅ ነኝ ቢል ወይም የማይደፈር መስሎ ለመቅረብ ቢሞክር ለነጻነቱ የቆረጠ ህዝብ ፊት ሲቆም ፀሐይ እንደገላመጠዉ በረዶ ሟምቶ የሚጠፋ ሀይል ነዉ።


### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org